# በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ያለው ፋይዳ

አሸናፊ ደበበ[1]

**አጠቃሎ፤** *የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ነው። ይህን ዓላማ ለመሳካት ጥናቱ ፍትነት መሰል ቅድመና ድሕረትምህርት ባለቁጥጥር ቡድን ንድፍን ተከትሏል። ለዚህም የቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የክፍል ደረጃው (አስረኛ ክፍልን) በአመቺ የንሞና ዘዴ፣ ሁለት መማሪያ ክፍሎችን (10B እና 10E) በቀላል የእጣ ንሞና ስልት እንዲሁም በመማሪያ ክፍሎቹ የሚማሩ 95 ተማሪዎች በጠቅላይ የንሞና ስልት በጥናቱ ተሳታፊነት ተመርጠዋል። ከ95 ተማሪዎች መረጃ የተሰበሰበው በቅድመና ድሕረትምህርት የሰዋስው እውቀት መለኪያ ፈተና ነው። አስተማማኝነቱን ለመፈተሽም በዋናው ጥናት ባልተሳተፉ ከ25 ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቦ የተገኘው መረጃ በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ ውጤቱን ከ0.7 በላይ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል። በቅድመትምህርት ፈተናው የተገኘው ውጤት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ስታትስቲካዊ ልዩነት ባለማሳየቱ ፍትነቱ ተካሂዷል። ከፍትነት በኋላ ተጠኚ ተማሪዎች የድህረትምህርት ፈተናውን ተፈትነዋል። በፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት የቁጥጥር ቡድን 12.563፣ የሙከራ ቡድን 14.404 ነው። በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ያለው ልዩነት ስታተስቲካዊ ጉልህ መሆኑን ለመፈተሽ በተደረገው የነጻ ናሙና ቲቴስት ፍተሻ በተገኘው ውጤት መሰረት ($t(93) = -3.462$, $P = 0.001$) በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። በመሆኑም ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት የሰዋስው እውቀትን የመጨመር ፋይዳ እንዳለው መረዳት ተችሏል። ማስተማሪያ ዘዴው የሰዋስው እውቀትን ከመጨመር አንጻር ያለውን የተጽዕኖ መጠን ለመፈተሽ በተደረገው የኮህን ዲ ፍተሻ ከፍተኛ ተጽዕኖ ($d = 0.71$) እንዳለው ማረጋገጥ ተችሏል። ከጥናቱ ውጤት በመነሳት መምህራን የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማዳበር ይዘት ተኮር ዘዴን ቢተገብሩ፣ በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወይም ማሻሻል ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች የሰዋስው ትምህርትን አቀራረብና ማስተማሪያ ዘዴ ሲያዘጋጁ ለይዘት ተኮር ዘዴ ትግበራ ምቹ የሆኑ አቀራረቦችንና ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢያካትቱ፣ በሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ምርምር ማድረግ የሚፈልጉ ተመራማሪዎች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ምርምር ቢያደርጉ የሚሉ የጥናት ጥቆማና አስተያየቶች በአጥኚው ቀርበዋል።*

***ቁልፍ ቃላት፤*** *የሰዋስው እውቀት እና ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት*

## *መግቢያ*

በቋንቋ ትምህርት ከሚሰጡ ይዘቶችና ከሚተኮርባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ሰዋስው ነው። በማንኛውም የስነ ልሳን ባለሙያ እምነት ከማንኛውም የክህሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊጨብጠው የሚገባ ጥልቅና ረቂቅ የሆነ የሰዋስው እውቀት አለ (ባየ፣ 2000)። ይህ የሰዋስው ትምህርት ደግሞ ረጅም እድሜ አለው። ከዛሬ 2400 አመታት

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛን ማስተማር (TeAm) መርኃግብር የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ

አስቀድሞ ግሪካዊው ፈላስፋ ፕሌቶ ዓረፍተ ነገርን ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ብሎ ከፋፍሎ እንዳሳየና ትምህርቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ እንደመጣ የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ (Anne, 2007)፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የሚመደብ ከመሆኑም ባሻገር ያለሰዋስዋዊ እውቀት ቋንቋን በትክክል መረዳትና ማወቅ እንደሚያስቸግር የምሁራን እምነት ነው (Anne, 2007)፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ለመገልገል በጣም አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

በርካታ ዘመናት ዘልቆ መጀመሪያ በላቲን በኋላም በግሪክ ቋንቋ ይዘወተር የነበረው የመጀመሪያው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ሰዋስው ወትርጉም የተሰኘው ነበር፡፡ ይህ ስነ ዘዴ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ ድረስ ስር ሰዶ የቆየ እንደነበረ የስነልሳን ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ (Rechards & Rodgers, 2001)፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን ተከትለው ሌሎች አዳዲስ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ብቅብቅ ያሉ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ዘዴ (Direct method) እና አዳምጦ የመናገር ዘዴ (Audiolingual) ገነው የታዩበት ነበር፡፡ በተለይም ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን ስንመለከተው የትምህርቱ ማቅረቢያ ዘዴ ሰዋስው እንደሆነ ስሙ ራሱ ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ታሪክ ትልቅ ቦታ ሲሰጠው የነበረ ነው፡፡

Rechards & Rodgers (2001) ቋንቋ ለማስተማር ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ዘዴዎች ባሻገር ተግባቦታዊ ዘዴ (Communicative based Instruction)፣ ተራክቧዊ የቋንቋ ማተማሪያ ዘዴ (Cooprative based Instruction)፣ ይዘት ተኮር ዘዴ (Content based Instruction)፣ እንዲሁም ተግባር ተኮር ዘዴ (Task based Instruction) በተለያየ ጊዜ ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የብዙ አጥኝዎችንና የቋንቋ አስተማሪዎችን ትኩረት እየሳበ የመጣው ይዘት ተኮር ዘዴ እንደሆነ Hardman (2009) እና Snow (1997) ይገልጻሉ፡፡ በእርግጥም ዘዴው ቋንቋን ለማስተማር በቀጥታ የቋንቋ ይዘቶችን ከማቅረብ ይልቅ ሌሎች ይዘቶችን በማቅረብ እንዲማሩ የሚያደርግ መሆኑ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ ቁልፍ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ የሰዋስው ትምህርትም እንዲሁ አንደቋንቋ ትምህርት ይዘት በይዘት ተኮር አቀራረብ ቢቀር ተመራጭ መንገድ ነው፡፡ በተለይም ከትምህርቱ ይዘት ባህርይ አንጻር የበለጠ ተግባራዊ ቢደረግ ተመራጭ መሆኑን Hardman (2009) ያስረዳሉ፡፡በተጨማሪም ባየ (2000፣xxi) ስለሰዋስው ሲያስረዱ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> በማንኛውም የቋንቋ ሥነልሳን ባለሙያ እምነት ከማንኛውም ክሂሎች ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባ ጥልቅ እና ረቂቅ የሆነ ዕውቀት አለ፡፡ ይኸውም የቋንቋ ሥርዓት ወይም ሰዋስው በመባል የሚታወቅ ክፍል ነው፡፡ ይህም ትምህርት የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሐረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው፡፡ ይዘቱ የሥርዓት ነው፤ ስለዚህም ከአጠቃቀም ይለያል፡፡

ከባየ ሀሳብ የምንረዳው የቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም ተነጣጥለው የሚታዩ እንደሆኑና የቋንቋውን ሥርዓትና ህግ የሚመለከተው ሰዋስው እንደሆነ ነው፡፡ ጌታሁን (1990) ደግሞ ሰዋስው ሁለት አሻሚ ፍችዎች እንዳሉት ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው በአዕምሮ ውስጥ ያለ የቋንቋ እውቀት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተማሪዎች ስለቋንቋ የሚያደርጉት ገለጻ ነው፡፡ የመጀመሪው ፍች ሁሉም ሰው ቋንቋውን መጠቀም የሚያስችለው ችሎታ እንዳለው የሚያስረዳ አዕምሯዊ እሳቤ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡ ሁለተኛው ፍች ደግሞ ከባየ ብያኔ ጋር ይበልጥ የሚቀራረብ ነው፡፡ ይህም ያንድን ቋንቋ ሥርዓት የሚመለከት በመሆኑ ከመጀመሪያው ፍች ለየት ይላል፡፡

በሌላ መልኩ Stern (1992)፣ Ur (1988) እና Harmer (1978) ሰዋስው ቃላት ተቀናጅተው ዓረፍተ ነገር የሚመሰርቱበት እና የቋንቋ ስርዓት የሚያጠና ቋንቋ ክፍል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሄ ሀሳብ ሰዋስው የቋንቋን የአወቃቀር ሥርዓት የሚያጠና መሆኑን ያስረዳል፡፡ የተለያዩ የቋንቋ አሀዶች በየደረጃቸው በመቀናጀት እስከትልቁ መዋቅር (እስከ ዓረፍተ ድረስ) ያለውን የአወቃቀር የሚመለከት ከሆነ ሰዋስው ይባላል ማለት ነው፡፡ ከዓረፍተ ነገር ከፍ እያለ ከሄደ ደግሞ ወደመጻፍ ክሂል ትምህርት ያመራል፡፡

Brown (1994) ሰዋስው የቋንቋ ሥርዓት መሆኑን በመግለጥ ያ ሥርዓት ግን በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ ይሁንታን ያገኘ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው የአንድ ቋንቋ ሥርዓት ወይም ህግ ህረተሰቡ ልክ ነው ብሎ የተቀበለው መሆን እንደሚኖርበት ነው፡፡ ሀሳቡ የቋንቋ አጠቃቀምንና የቋንቋ ሥርዓትን ሊያቀራርብ የሚችል ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ባየ (2000) እና Brown (1994) የቋንቋ ሥርዓት ተናጋሪዎቹ የሚጠቀሙበት አገባብ ልክ ነው ወይም የተሳሳተ ነው ማለት የሚያስችላቸው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሀሳቡን ስናጤነው "ልክ ነው" ወይም "ልክ አይደለም" የሚሉት የቋንቋው ተናጋሪዎች እንደመሆናቸው መጠን ሥርዓቱ ከቋንቋው ተጠቃሚዎች እንደሚቀዳ ያሳየናል፡፡ ይህም ከBrown ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡

የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ Stern (1992) እንደሚያስረዱት የተለያዩ የሀሳብ መለያየቶች አሉ፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል ቢባልም መካተት የለበትም የሚል ሙግት እንደቀረበበትም አይዘነጋም፡፡ ይህን አስመልክቶ Bygate እና ሌሎች (1994) በአፍ መፍቻ፣ በሁለተኛ ቋንቋም ይሁን በውጭ ቋንቋ ትምህርት በይዘትነት መቅረብ አለበት ወይም የለበትም የሚል ውዝግብ ሲያስነሳ እንደኖረ ጠቅሰዋል፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት ያስፈልጋልና አያስፈልግም የሚል ሲሆን ለ2000 ዓመታት ሲያከራክር ቆይቷል፡፡ ምሁራኑ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ አመክንዮ በመያዝ በርካታ ሀሳቦችን በማንሳት የተከራከሩ ሲሆን ሀሳባቸውን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው በሶስት ጎራ ይመደባል፡፡

የመጀመሪያው ጎራ ሰዋሰው በትምህርትነት መሰጠት አለበት የሚሉ ሲሆኑ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች ይልቅ የሰዋስው ትምህርት ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት አበክረው ይከራከራሉ፡፡ ስለሆነም ይህን ሀሳብ በሚያራምዱ ወገኖች አመለካከት የትምህርት ዋናና ተቀዳሚው ግብ የተማሪዎችን የሰዋስው ብቃት ማዳበር ነው፡፡ ሁለተኛው ጎራ ደግሞ ከሰዋስው ትምህርት ይልቅ ለቋንቋ ተግባቦት ልዩ ትኩረት መሰጠት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ሀሳባቸውን የሚያራምዱትም ከቋንቋ ትምህርት ዐብይ ዓላማ በመነሳት ነው፡፡ ቋንቋ ለተናጋሪው መግባባት ባለበት መጠን ያግባባ ዘንድ ማስተማር ስላለብን ተማሪዎቹ የሚማሩትም ተግባቦትን ነው ይላሉ፡፡ ሶስተኞቹ ደግሞ ሁለቱንም ሀሳቦች ሊያስታርቅ የሚችል ሀሳብ አንስተዋል፡፡ ይህም “የቋንቋ ትምህርት ስኬታማ የሚሆነው ሰዋስውንም ሆነ ተግባቦታዊ ክንውኖችን በማቀናጀት ስናስተምር ነው” ሲሉ ያስረዳሉ (Stern 1992)፡፡

በአሁኑ ዘመን የበለጠ እየተሰራበት ያለና ተቀባይነት ያገኘው ሀሳብ ሁለቱን አቀላቅሎ ማስተማር የሚለው ነው፡፡ የቋንቋን ሥርዓት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ሰዋስውን ይማራሉ፤ ያወቁትን ሥርዓት በደንብ እንዲጠቀሙበት ደግሞ ለተግባቦት የሚጠቅሙ ትምህርቶችን እናስተምራቸዋለን፡፡ ይህን በተመለከተ ጌታሁን (1990፣v) ሲገልፁ “የቋንቋ ትምህርት ዓላማ በክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በስርዓት ላይም መሆን አለበት” ይላሉ፡፡ ምክኒያቱም ሁለቱም አንድ ቋንቋን ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸውና፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምሬአለሁ የሚለው ሰው እውቀት ቁንፅል ይሆናል ብለዋል፡፡ ይህም ክሂላቱም ሆኑ የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋ ትምህርት አስፈላጊዎች እንደሆኑ አመላካች ነው፤ የሰዋስው ትምህርት ከክሂል ትምህር ተለይቶ ሊታይ እንደማይገባው ያሳያል፡፡ ምክኒያቱም አንድ ሰው ሲፅፍ እና

ሲናገር የሚያሣየውን ስህተት ወይም ትክክለኛነት በመገምገም ለስህተቱም ሆነ ለትክክለኛነቱ ምክኒያት ለማቅረብ ቋንቋውን ከማወቅ አልፎ የቋንቋውን ስርዓት ማወቅና በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የክሂል መለኪያ መስፈርቱ ሰውስው መሆኑን ያመለክታል፡፡

የተገለጸው ውዝግብ ቢኖርም በትምህርትነት ከመቅረብ አልተገደበም፡፡ ከትምህርትነት እንዲገለል ያልተደረገበት ጉዳይም ለአጠቃላዩ የቋንቋ ትምህርት ጉልህ ሚና ስላለው ነው፡፡ ባየም (2000) የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ብቻ ካወቀ ተማሪ በተሻለ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ እውቀት እንዳለው ገልጸዋል፡፡ ይህም የክህሎት ትምህርት የተቃና የሚሆነው ከሰዋስው ትምህርት ጋር አብሮ ሲቀርብ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በፊት በነበረው የሰዋስው ትምህርት ታሪክ በየዘመናቱ የፈለቁት ንድፈ ሀሳቦች ሰዋስውን ከክሂላት ጋር አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያዳግቱ ነበሩ፡፡

የአንድን ትምህርት ይዘት የምናቀርበው ቋንቋ በመጠቀም ነው፡፡ ማንኛውም ይዘት ካለቋንቋ መቅረብ አይችልም፡፡ ማንኛውም ይዘት ካለቋንቋ መቅረብ አይችልም፡፡ ቋንቋም ይዘትን ተሸክሞ ወደተፈለገው ቦታ ለማድረስ ያስችላል፡፡ ይህ ተመጋጋቢነታቸው ደግሞ በትምህርቱ ዓለም ላይም የሚከሰት ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት በእውነተኛው ዐውድ ውስጥ በማስገባት የሚሰጥ ከሆነ ትምህርቱ እንዲሰርጽ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡ ስለዚህ ቋንቋን ለማስተማር ይዘቶችን መጠቀም ለትምህርቱ ስኬታማነት ወሳኝ ነው (Hardman 2009)፡፡ ይህ መሆን የሚችለው ደግሞ ሰዋስዋዊ ህግጋቱ ሳይፋለስ ሊባል የተፈለገውን ነገር ማንጸባረቅ ሲቻል ነው፡፡

ሰዋስው አንዱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል እንደመሆኑ መጠን ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማስተማር እንችላለን፡፡ በዚህ ዘዴ ሰዋስውን ስናስተምር ትኩረት የምናደርገው ሰዋስው በተለያዩ አሃዶች ውስጥ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ላይ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በራሳቸው ስራ ላይ ወይም በሌሎች አሃዶች ላይ ያለውን ሰዋስዋዊ ሁኔታ እንዲያዩ ያደርጋል፡፡ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር ከሌሎች የተለመዱ የሰዋስዋዊ ዘዴዎች ልዩ የሚያደርገውም በዓረፍተ ነገር ደረጃም ብቻ ሳይሆን በአንቀጽ ወይም በውህድ አሃድ ላይ ያለውን ሰዋስዋዊ ሁኔታ አግባባዊ በሆነ መልኩ መገንዘብ ማስቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም በሰዋስው ትምህርት ለተማሪዎች ሐሳብና አስተምህሮን እንዲሁም ትርጉም ያለው አውድን ለመፍጠር ያስችላቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በይዘት ተኮር ዘዴ የሰዋስው ትምህርት ሲሰጥ ብቻውን አይመጣም፡፡ ጎን ለጎንም የቋንቋውን መድበለ ቃላት ፍቺ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ ይዘት ተኮር ዘዴን በመጠቀም ሰዋስውን ማስተማር የትኩረት ነጥቡ ይዘትና የቋንቋ ቅርፅን አቀናጅቶ ማቅረቡ ላይ ስለሚሆን አካዳሚያዊ (ትምህርታዊ ተግባሩ) ሰዋስውን ከይዘት ጋር በማገናኘት በንፅፅር ማሳየቱ ላይ ይሆናል፡፡

ይሁን (2013) እና ሽፈራው (2013) ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ተስፋዬ (2012) ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ውበቱ (2011) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ እንዲሁም ሌሎች አጥኚዎችም ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር ተቀራራቢ ጥናቶችን አጥንተዋል፡፡

ይሁን (2013) እና ሽፈራው (2013) ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት በማድረግ ዘዴዎቹ የሰዋስው እውቀትን እንደሚጨምሩ አሳይተዋል፡፡ በተመሳሳይ ተስፋዬ (2012) ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም አዎንታዊ ፋይዳ እንዳላቸው፣ ውበቱ (2011) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እንደሚጨምር አሳይተዋል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ ሌሎች አጥኚዎች ያላዩት ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ ማስተማር የሰዋስውን እውቀት ከመጨመር አንጻር ያለው ፋይዳ ተፈትሿል፡፡

በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ጥናት ጋር ይቀራረባሉ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ስር ሰዋሰውን መሰረት ያደረጉ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ ማስተማር ላይ ግን የተሰራ ጥናት አልታየም፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ትኩረት በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፡፡

Ur (2006) የቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን በሚገባ እንዲጠቀም የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊና ወሳኝ እንደሆነ ሲያስረዱ Cunningsworth (1995) ሰዋስውን ያላካተተ መማር ማስተማር ሂደት የተሟላ ነው ለማለት እንደሚያስቸግር ገልጸዋል፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ተዘጋጅቶ መቅረቡ ምን ያህል አስፈላጊ እና ወሳኝ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ርቱዕነት በልማድ ሊገኝ ይችላል፡፡ ትክክለኛነትን ለማግኘት ግን ቋንቋውን ስርዓት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የቋንቋውን ስርዓት ለማወቅ ደግሞ የሰዋስው ትምህርቱን ወይም ስርዓቱን መማር አስፈለጊ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ ቢሆንም በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የተማሪዎች የሰዋስው እውቀት ማነስ ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ነው (ሙሉጌታ፣ 1996፤ ዮሐንስ፣ 2003፤ አዲስዓለም፣ 2012)፡፡

ሙሉጌታ (1996) የሰዋሰው ትምህርት ክፍል ውስጥ ስላለው አተገባበር፣ ዮሐንስ (2003) የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ አተገባበር ግምገማ እና አዲስዓለም (2012) የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉት ድርሰት ላይ የሚስተዋሉ አሉታዊ የሰዋስው ተጽዕኖዎች እና የግድፈት ምንጮች ፍተሻ ሲያጠኑ የተማሪዎች የሰዋስው እውቀት በጣም ዝቅ ያለ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ አሚናት (2016) ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት በርከት ያለ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን እንደፈጸሙ በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡ ከአጥኚው ልምድ አንጻርም በተለያዩ ተከታታይ ጊዜያት ተማሪዎች ሰዋስውን በቀጥታ ከተማሩ በኋላ፣ በምዘና ወቅት ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ስነ ዘዴ በተለይ ይዘት ተኮርን በመጠቀም ኢቀጥተኛ በሆነ መልኩ ሰዋስውን ማስተማር ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ ለመፈተሽ ጥናቱን ለማከናወን ተነስቷል፡፡

በመሆኑም ጥናቱ ሁለት መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተጠንቷል፤ ጥያቄዎቹም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

1. በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?
2. ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?

## የአጠናን ዘዴ

### የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ፍትነትመሰል (quasi-experimental) የተሰኘውን ንድፍ ተከትሏል፡፡ በዚህም መሰረት ቅድመና ድሕረትምህርት ባለቁጥጥር ቡድን (quasi-experimental pretest-posttest comparison group) ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### የጥናቱ ተሳታፊዎች

በዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት በ2016 ዓ.ም. በቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ የክፍል ደረጃ ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ስድስት ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል የቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ አጥኚው በዚሁ ትምህርት ቤት ለበርካታ አመታት በመምህርነት ሙያ አገልግሏል፤ እያገለግልም ይገኛል፡፡ መረጃ ለማግኘት ካለማስቸገሩና ስለተማሪዎቹ አጠቃይ መረጃ ለማግኘት የተጠቀሰው ትምህርት ቤት ተመራጭ በመሆኑ በአመቺ የንሞና ስልት በጥናቱ ተካቷል፡፡

በቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ ጥናቱ ሲከናወን ተጠኝ ሆነው የተመረጡት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህ የክፍል ደረጃ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ለተከታታይ ዓመታት ሲያተምር በአስረኛ ክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ ያገኘው በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የክፍል ደረጃ በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡

በጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሆኑት በ2016 ዓ.ም. በቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ የክፍል ደረጃ ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲማሩባቸው የነበሩ አምስት መማሪያ ክፍሎች ሲሆኑ በአምስቱም መማሪያ ክፍሎች 281 ተማሪዎች አሉ፡፡ የሙከራ ጥናቱን ለማጥናት ይመች ዘንድ ከአምስቱ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ክፍሎች ቀላል የእጣ ናሙና ስልትን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡

የተመረጡ ክፍሎች 10B እና 10E ናቸው፡፡ አንዱ ክፍል ደግሞ ለሙከራ ጥናት (Pilot Study) ደግሞ 10A ተመርጧል፡፡ ለዋናው ጥናት የተመረጡ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛት ከ10B 48 ተማሪዎች ከ10E ደግሞ 47 ተማሪዎች (በድምሩ 95 ተማሪዎች) ተመድበዋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በጠቅላይ የንሞና ስልት የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡

## መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የጥናቱን ዓላማ ግብ ለመምታት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ፈተና ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ፈተናው የተዘጋጀው የክፍል ደረጃውን መርሃ ትምህርት መሰረት በማድረግ ያደረገ ሆኖ የተዘጋጁት ጥያቄዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ አወቃቀርን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የፈተና ይዘቶች በዓረፍተነገር ክፍሎች (ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ማሰሪያ አንቀጽ)፣ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚታዩ የተለያዩ ስምምነቶች (የቁጥር፣ የጾታ፣ የጊዜ፣ የመደብ)፣ የቃላት ቅድም ተከተላዊ አቀነጃጀት፣ በቃል ክፍሎችና በሐረጎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑና ስነፍቺን መሰረት ያደረጉ 20 ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የተዘጋጀው ፈተና በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ሁለት ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ በቅድመ ትምህርት ወቅት የተሰጠው ፈተና ዓላማ በጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የተማሪዎቹን የሰዋስው እውቀት ዳራ ተመጣጣኝ እንደነበር ለመፈተሽ ነው፡፡ የድህረ ትምህርቱ ፈተና ዓላማ ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ከተማሩ በኂላ ስነዘዴው በተማሪዎች የሰዋስው እውቀት መሻሻል ላይ የሚያሳድረውን አስተዋጽኦ ለመርመር እንዲሁም የተጽኖውን መጠን ለመፈተሽ አገልግሏል፡፡

የቅድመና የድህረትምህርት ፈተናው ለታለመለት ዓላማ ከማገልገሉ በፊት በጥናቱ አማካሪ፣ በቋንቋ መምህራን አስተያየት ተሰጥቶታል፡፡ ከዚያም የፈተናውን አስተማማኝነት ለመፈተሽ በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች የሙከራ ጥናት (pilot study) ተካሂዶበታል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ቁጥር 25 ሲሆን ፈተናውን ተፈትነው ያገኙት ውጤት በክሮንባህ አልፋ ቀመር ተሰልቷል፡፡ በስሌሉቱ መሰረት ውጤቱም $\alpha$=.789 ሆኗል (የፈተናውን አስተማማኝነት ለመለካት ያገለገለው መረጃ በአባሪ 2 ላይ፣ ስሌቱ አባሪ 7 ላይ ተመልክቷል)፡፡

ይህም መረጃ ለመሰብሰብ አስተማማኝ በመሆኑ ፈተናውን ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡

### የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት

የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍና የመምህር መምሪያ ተምረዋል፡፡ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ግን የማስተማሪያ ማኑዋል ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ የማስተማሪያ ማኑዋሉ ይዘቶች የተካተቱት ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ እና ከመርሀ ትምህርቱ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ለክፍል ደረጃቸው የሚመጥን ይዘት የሚገኘው ከመማሪያ መጽሐፉና ከመርሀ ትምህርቱ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚያም ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሚመለከቱ ከተዳሰሱ ንድፈ ሀሳባዊ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የማስተማሪያ ማኑዋሉ ተዘጋጅቷል፡፡

በይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በቅድመ ትግበራ፣ በትግበራ ጊዜማ በድህረ ትግበራ የሚከናወኑ ተግባራት በማስተማሪያ ማኑዋሉ ላይ ተካተው ተዘጋጅተዋል፡፡ በቅድመትምህርት ትግበራ ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያመች የተለያዩ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን በክለሳ ድርሳናት ላይ ተገልጿል፡፡ በዚህ ጥናት ከመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና ከቁሳቁሶች አቅርቦት አንጻር ተግባራዊ የተደረገው ምንባብንና ዲስኩርን መጠቀም ነው፡፡ ስለሆነም የክፍል ደረጃቸውን የሚመጥኑና የማስተማሪያ ዘዴውን ለመተግበር የሚያግዙ ምንባቦች፣ ምልልሶችና ዓረፍተነገሮች ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም በማስተማሪያ መሳሪያው አማካይነት የሰዋስው ይዘቶችንና አጠቃቀማቸውን እንዲለዩ የሚያደርጉ ተግባራትም ተካተው ቀርበዋል፡፡ በተዘጋጀው ማኑዋል አማካይነት የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ በጥንድና በቡድን ውይይት፣ በግል ሥራዎች፣ በቤት ወሰድ ሥራዎችና በመሳሰሉት ትምህርቱ ቀርቧል፡፡

## የመረጃ መተንተኛ ስልት

ፈተናው በአጥኚው ታርሞና ውጤቱ ተመዝግቦ የነጻ ናሙና ቲቴስትና የኮህን ዲ (Cohen's d) ስሌቶች አማይነት ተተንትነዋል፡፡ የነጻ ናሙና ቲቴስት በቅድመና በድህረትምህርት በሙከራና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር እንዲሁም ኮህን ዲ ነጻ ተላውጠው በጥገኛ ተላውጦዎች ላይ ያስገኘውን የተጽእኖ መጠን ለማስላት አገልግሏል፡፡

በመሆኑም በፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን በመከተል ተተንትነዋል፡፡

ከትንታኔው አስቀድሞ ስለሰዋስው እውቀት የተመዘገቡ ውጤቶች ውስጥ ፍንግጥ ነጥቦች አለመኖራቸው በባለሳጥን ግራፍ ተሰርተው ፍንግጥ ነጥቦች እንደሌሉ ተረጋግጧል (የባለሣጥን ግራፎችን ከአባሪ 12 እና ከአባሪ 13 ላይ ይመልከቱ)፡፡ በኋላም የነጻ ናሙና ዋና እሙን የሆነውን የውጤቶች መደበኛ ሥርጭት መሟላቱን በተደጋጋሬ አምድ ግራፎችና በሻፒሮ ዊልክ አማካይነት ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ከአባሪ 8 እና 9 ላይ እንደተመላከተው የተገኙ የሻፒሮ ዊልክ ውጤቶች ከ0.05 በላይ ($P > 0.05$) በመሆናቸው መደበኛ ስርጭቱን ያሟሉ እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የተደጋጋሬ አምድ ግራፉ እንደሚያሳየው የተመዘገቡ ውጤቶች አንጻራዊ የሆነ የሥርጭት ወጥነት እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መረጃዎቹ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረታዊ እሙን የሆነውን የስርጭት ወጥነት አሟልተው እንደተገኙ በተገለጸው መንገድ ከተፈተሸ በኋላ በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖች የቅድመትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከልና በሁለቱ ቡድኖች የድህረትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማወቅ ሲባል መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ ነጻ ተላውጦው (ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ) በጥገኛ ተላውጦው (የሰዋስው እውቀት) ላይ ያስገኙትን የተጽእኖ መጠን (effect size) በኮህን ዲ ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

## የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ቀዳሚ ጥያቄ "በይዘት ተኮር ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር  የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?" የሚል ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሲባልም ፍትነቱ በሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከመተግበሩ በፊት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከሰዋስው እውቀት አንጻር ተመጣጣኝ መሆን አለመሆናቸውን ለመፈተሽ አንድ አይነት የቅድመትምህርት የሰዋስው እውቀት መለያ ፈተና ተፈትነው ውጤታቸው ተመዝግቧል (የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት ፈተና ውጤቶችን ከአባሪ 3 እና 4 ላይ ይመልከቱ)፡፡ በቅድመትምህርት የሰዋስው እውቀት ፈተና ከሁለቱ ቡድኖች የተገኙት መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲቴስት ተፈትሸው የተገኙት ውጤቶች በሰንጠረዥ 1 ላይ ተገልጿል፡፡

ሰንጠረዥ 1፦ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 48 | 12.125 | 2.523 | -0.670 | 93 | 0.505 |
| የሙከራ | 47 | 12.532 | 3.348 | | | |

በሰንጠረዥ 1 ላይ እንደተገለጸው በቅድመትምህርቱ የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት ጋር ሲነጻጸር በ0.407 በልጦ ተገኝቷል። በመደበኛ ልይይትም በተመሳሳይ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር በ0.825 በልጠዋል። ይህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የታየው የሰዋስው ፈተና ውጤት ልዩነት ስታትስቲክሳዊ ጉልህነት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመፈተሽ ሲባል መረጃዎቹ በነጻ ናሙና ቲቴስት ተፈትሸዋል፤ የተገኘው ውጤትም t(93) = -0.670, *p* = .505 ነው። በቲቴስት ፍተሻው በተገኘው ውጤት መሰረት በቁጥጥር ቡድን ተማዎችና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ስታትስቲክሳዊ ልዩነት የላቸውም። በዚህም ሙከራው ከመካሄዱ በፊት ሁለቱ የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች በሰዋስው እውቀት ተመጣጣኝ እንደነበሩ መረዳት ተችሏል።

የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የሰዋስው አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት ከሙከራው አስቀድሞ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ተመጣጣኝ እንደነበሩ በሰንጠረዥ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት ተረጋግጦ የሙከራ ትግበራው ተተግብሯል። ከትግበራው በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ የድህረትምህርት የሰዋስው እውቀት ፈተና ተፈትነው በውጤቶቻቸው መካከል ያለው ልዩነት በነጻ ናሙና ቲቴስት ተፈትሿል፤ የቲቴስት ውጤቱም በሰንጠረዥ 2 ተገልጿል (የሁለቱ ቡድኖች የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች ከአባሪ 5 እና ከአባሪ 6 ላይ ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 2፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 48 | 12.563 | 2.492 | -3.462 | 93 | 0.001 |
| የሙከራ | 47 | 14.404 | 2.692 | | | |

ሰንጠረዥ 2 እንደተገለጸው ከአማካይ ውጤት አንጻር የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በ1.841 ይበልጣሉ። በመደበኛ ልይይትም በተመሳሳይ የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በ0.2 ይበልጣሉ። በእርግጥም ልዩነታቸው ስታተስቲካዊ ጉልህ መሆኑን ለመፈተሽ በሁለቱ ቡድን ተሳታፊዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተፈትሿል። የተገኘው ውጤትም $t(93) = -3.462$, $P = 0.001$ ነው፤ ውጤቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የፍትነቱ ቡድን በልጦ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የተማሪ መጽሀፍ እና የመምህር መምሪያ መሰረት፣ የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ደግሞ በይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አማካይነት ሰዋስውን ተምረው ሙከራው እንደተጠናቀቀ፤ የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በአማካይ ውጤታቸው በልጠው በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ማሳየታቸውን ያመለክታል። ለዚህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ለታየው የሰዋስው እውቀት ውጤት ልዩነት ምክንያቱ የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ አማካይነት መማራቸው እንደሆነ መረዳት ተችሏል።

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ “ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?” የሚል ነው። በጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ የተገኘው ውጤት ይዘት ተኮር የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የሰዋስው እውቀት ላይ ለውጥ አምጥቷል። ሆኖም ግን የቲቴስት ውጤቱ ለውጥ እንዳመጣ እንጂ የለውጡ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አይጠቁምም። ለዚህም ተጨማሪ ፍተሻ አስፈልጓል።

ይዘት ተኮር ዘዴ በተማሪዎች የሰዋስው ችሎታ ላይ ያሳደረውን የተጽእኖ መጠን ለመፈተሽ አገልግሎት ላይ የዋለው የኮህን ዲ ቀመር ነው፡፡ በፍተሻውም ውጤቱም d = 0.71 ሆኗል፡፡ ይህም ይዘት ተኮር ዘዴ በተማሪዎች የሰዋስው ችሎታ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡

## የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ነበር፡፡ ለፍተሻውም የተተኳሪ ተማሪዎችን የሰዋስው እውቀታቸውን ለመለካት በተዘጋጀው የሰዋስው ፈተና ተሰብስቦ የነጻ ናሙና ቲቴስትና የኮህን ዲ ስሌቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ "በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?" የሚል ሲሆን በሰዋስው ፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የነጻ ናሙና ቲቴትስ ትንተና ተደርጓል፡፡ በትንተናው ውጤት መሰረት ($t(93) = -3.462$, $P = 0.001$) ነው፡፡ ውጤት $P<0.05$ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት እንዳለ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ከሙከራው (ከትምህርቱ) በኋላ ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑ ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከማሳደግ አንጻር የጎላ ፋይዳ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት Hardman (2009) ይዘት ተኮር ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር ለሰዋስው እውቀት ጉልህ ሚና እንዳለው ከገለጹት ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት ይሁን (2013) እና ሽፈራው (2013) ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ተስፋዬ (2012) ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ውብቱ (2011) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ካጠኑት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የተጠቀሱት ጥናቶች ሰዋሰውን ለማስተማር የተጠቀሙባቸው ብልሀቶች

ለሰዋስው እውቀት መጨመር ፋይዳ እንዳላቸው የገለጹ ሲሆን የፋይዳቸው መጠን ግን የተለያዩ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህም ሰዋስውን ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን እንዳስፈላጊነቱና እንደምናስተምረው ይዘት ባህርይ እየቀያየርን መጠቀም የሚኖረውን ፋይዳ የሚጠቁም ነው፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ "ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?" የሚል ነው፡፡ የተጽዕኖውን መጠን ለማጥናት በፈተናዎቹ የተገኙ አማካዮችን፣ መደበኛ ልይይቶችንና የናሙና መጠኖችን በመጠቀም የኮህን ዲ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በፍተሻውም ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከማሳደግ አንጻር ያለው ፋይዳ ጠንካራ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ጥናቶች ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች የተሻለ ተጽዕኖ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት Grabe and Stoller (1997) ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከመጨመር አንጻር ያለውን ፋይዳ ከገለጹት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ፋጡማ (2013) ሰዋስዉን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙ እና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከማዳበር አንጻር ያለውን ፋይዳ መርምረው ጠንካራ ፋይዳ እንዳለው ከገለጹት የጥናት ውጤት ጋር የሚቀራብ ግኝት ተገኝቷል፡፡

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ነው፡፡ በውስጡም በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽና ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል መሆኑን መመርመር የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎችን ይዟል፡፡ ለዚህም ፍትነት መሰል የጥናት ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የክፍል ደረጃው (አስረኛ ክፍልን) በአመቺ የንሞና ዘዴ፣ ሁለት መማሪያ ክፍሎችን (10B እና 10E) በቀላል የእጣ ንሞና ስልት እንዲሁም

በመማሪያ ክፍሎቹ የሚማሩ 95 ተማሪዎች በጠቅላይ የንሞና ስልት በጥናቱ ተሳታፊነት ተመርጠዋል፡፡ ከ95 ተማሪዎች መረጃ የተሰበሰበው በቅድመና ድሕረትምህርት የሰዋስው እውቀት መለኪያ ፈተና ነው፡፡ ፈተናው ከተጠኚዎች መረጃ ለመሰብሰብ ከማገልገሉ በፊት በአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በጥናቱ አማካሪ ታይቶ ማስተካከያ ተሰጥቶታል፡፡ አስተማማኝነቱን ለመፈተሽም በዋናው ጥናት ባልተሳተፉ ከ25 ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቦ የተገኘው መረጃ በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ ውጤቱን ከ0.7 በላይ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡

ከፍትነቱ በፊት ሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ፈተናውን ተፈትነው በተገኘው ውጤት አማካይነት ተመጣጣኝ ውጤት እንደነበራቸው በነጻ ናሙና ቲቴስት ፍተሻ ተፈትሿል፡፡ ከዚያም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉና በመምህር መምሪያ ባለው የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴ አማካይነት፣ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አማካይነት የሰዋስው ትምህርትን ተምረዋል፡፡ በመጨረሻም የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በሰዋስው ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ከተመዘገቡ በኋላ በነጻ ናሙና ቲቴስት ተሰልቷል፡፡

በትንታኔው መሰረት ከአማካይ ውጤት አንጻር የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች የላቀ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የውጤት ልዩነታቸው ስታተስቲካዊ ጉልህ መሆኑን ለመፈተሽ በሁለቱ ቡድን ተሳታፊዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር የፍትነቱ ቡድን በልጦ ጉልህ ልዩነት ($t(93) = -3.462$, $P = 0.001$) መኖሩን አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ ይዘት ተኮር ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከማሳደግ አንጻር ያለውን የተጽዕኖ መጠን ለመፈተሽ በተደረገው የኮህን ዲ ፍተሻ ከፍተኛ ተጽኖ እንዳለው ($d = 0.71$) የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

## የመፍትሄ ሀሳብ

የዚህ ጥናት አጥኚ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አስተያየቶችና የጥናት ጥቆማ አቅርቧል፡፡

1. በጥናቱ ግኝት እንደቀረበው ይዘት ተኮር ዘዴን ተጠቅሞ የሰዋስው ትምህርትን ማተማር የሰዋስው እውቀትን ከማዳበር አንጻር ጉልህ የሆነ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም የቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የተማሪ

መጽሀፍ እና የመምህር መምሪያ መሰረት፣ የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ደግሞ በይዘት ተኮር ዘዴ አማካይነት በመማራቸው ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማዳበር ይዘት ተኮር ዘዴን ቢተገብሩ፤

2. ይዘት ተኮር ዘዴ አተገባበር ከተለመደው የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ለየት ባለ አቀራረብ የሚቀርብ ነው፡፡ በመሆኑም በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወይም ማሻሻል ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች የሰዋስው ትምህርትን አቀራረብና ማስተማሪያ ዘዴ ሲያዘጋጁ ለይዘት ተኮር ዘዴ ትግበራ ምቹ የሆኑ አቀራረቦችንና ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢያካትቱ፤

3. ይህ ጥናት የተደረገው አማርኛን እንደአፍመፍቻ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ምርምር ማድረግ የሚፈልጉ ተመራማሪዎች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ምርምር ቢያደርጉ፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ሙሉጌታ ይታየው፡፡ (1996)፡፡ *የተማሪ ተኮር ማተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮተቤ መምህራን ትምህረት ኮሌጅ የሰርተፊኬት መርሃ ግብር እንደታየው፡፡* አማርኛን በመማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ፡፡

ሽፈራው አቅናው፡፡ (2013)፡፡ *ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማሻሻል ያላቸው ሚና፤ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፤ ጎንደር፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2000)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፤ የት.መ.ማ.ማ.ድ.፡፡

ተስፋዬ ለገሰ፡፡ (2012)፡፡ *ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ መገምገም፡* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤ ደብረ ብርሃን፡፡

አሚናት መሀመድ፡፡ (2016)፡፡ *በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት (በእኖር ኤነር መገር ወረዳ የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት)፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ፡፡

አዲስዓለም ዘሪሁን፡፡ (2012)፡፡ *የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፏት ድርሰት ላይ የሚስተዋሉ አሉታዊ የሰዋስው ተጽዕኖዎች እና የግድፈት ምንጮች ፍተሻ፡፡* አማርኛን በመማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ባሕር ዳር፡፡

ውበቱ በዛብህ፡፡ (2011)፡፡ *ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት (በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)*፡፡ አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤ ደብረ ብርሃን፡፡

ይሁን ተስፋዬ፡፡ (2013)፡፡ *ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስውን የመማር ተነሳሽነት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፤ ጎንደር፡፡

ዮሐንስ አያሌው፡፡ (2003)፡፡ *“የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ የአተገባበር ግምገማ (በሰሜንወሎ ዞን በሚገኙ ሁለት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች)፡፡* አማርኛን በመማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ (1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡* አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Anne, S. (2007). *Basic English Grammare For English Language Learners*. USA፡ Saddleback Education Publisher.

Brown, D. (1994). *Principle of Language Learning and Teaching*. USA: Prentice Hall.

Bygate, M., Alan, T. and Eddie, W. (1994). *Grammar and Language Teacher.* Hempstead Printice Hall.

Cunningsworth, A. (1995). *Choosing Your Course Book.* Oxford: Heinemann.

Hardman, M. C. (2009). "Developing A Teachers' Handbook for Content based Instruction at Brigham Young University's English Language Center". in partial fulfillment of the requirements for the degree of Master of Arts. Brigham Young University. (Unpublished).

Harmer, I. (1978). *Teaching and Learning Grammar*. Hong ong. london.

Richards, J., & Rodgers, T. (2001). Approaches and Methods in *Language Teaching* (p. 204). New York: Cambridge University Press.

Snow,M.A.(2001). Content Based and Immersion Module for Second and Foreign Language Teaching.

Stern. H.H (1992) *Grammar Practice Activities*: *Apractical Guide For Teachers.* Cambridge: Cambridge university press.

Ur, P. (1988). *Grammar Practice Activity Approach Guide For Teachers*. Cambridge. Cambridge university press.

Ur, P. (2006). *A Course in Language Teaching practice and theory*. ($13^{th}$ edition). Cambridge: Cambridge University Press.